


# ድምፅ



ቅጽ 1 ቁጥር 5 ሚያዝያ 19 1998 ዓ.ም / April 27 2006 / ገጽ 1

## ርዕሰ ዜና

- ምርጫ ቦርድ ለተለጣፊው ቅንጅት ሰርተፊኬት ሰጠ
- ቆራጥ የአዲስ አበባ ተመራጮች ደባውን አከሸፉ
- ብርቱካን ሚዴቅሳ ለአምባሳደር ቪኪ ኸድልስተን ደብዳቤ ፃፉ::
- በቃሊቲ ፖሊሶች በግምገማ ተወጥረዋል::

## የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ የግንቦት 97ቱን ምርጫና ምርጫውን ተከትሎ በሀገራችን የተከሰተውን የዲሞክራሲ አፈና አንደኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ፤ ታላቅ የሰላማዊ ሰልፍ ለግንቦት 8 (May 16 2006 ) አዘጋጅቷል::

ይህ ሰልፍ በግንቦት 7ቱ ምርጫ ማግስት፤ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ውስጥ ታይቶ የነበረውን ትንሽ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ፤ እስከነ አካቴው ያዳፈነበት ክስተት ለማስታወስና ለዓለምም ህዝብ ለማሳወቅ እንዲረዳ ተብሎ የተዘጋጀ ነው::

በዚሁ ሰልፍ ላይ፤ ማንኛውም የዲሞክራሲና ሰላም ደጋፊ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲገኝ ተጋብዟል::

## ሀገር ቤት

### ምርጫ ቦርድ ለተለጣፊው ቅንጅት ሰርተፊኬት ሰጠ

የምርጫ ቦርድ ለተለጣፊው ቅንጅት የዕውቅና ሰርተፊኬት መስጠቱን አስታወቀ:: ይሁንና፤ በምርጫ ቦርድና በነአቶ ተመስገን ዘውዴ መሀከል ያለመግባባት ያለ ይመስላል:: ተለጣፊውን ቅንጅት ምርጫ ቦርዱ አዲስ ሲለው ፕሬዝደንት ተብለው የተመረጡት አቶ ተመስገን ዘውዴል በበኩላቸው ዕውቅና ያገኘው የቀድሞው ቅንጅት እንጂ አዲስ የተቋቋመ ቅንጅት የለም ብለዋል:: ሆኖም፤ አቶ ተመስገን ዘውዴ፤ ተለጣፊው ቅንጅት የህዝብ ድጋፍንና በእስር የሚገኙ መሪዎችን ይሁንታ ማግኘት ለምን እንደተሳነው አላብራሩም:: በሌላ በኩል የምርጫ ቦርድ የፓርቲ ምዝገባ ክፍል ሀላፊ አቶ መኮንን ወንድሙ በማያሻማ ሁኔታ አሁን የተቋቋመው ቅንጅት አዲስ መሆኑን አረጋግጠዋል::

ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት፤ ተለጣፊው ቅንጅት ምርጫ ቦርድ የወሰነለትን የ1500 ሰዎች ፊርማ ማሟላት ባይችልም፤ በኢህአዴግ ጣልቃ ገብነት ሰርተፊኬቱን ለማግኘት ችሏል::

ቀደም ሲል፤ በእስር የሚገኙት የቅንጅት መሪዎች የወከሏቸው አራት አባላት በተራ አስተዳደራዊ ምክንያት፤ የምርጫ ቦርድ ሰርተፊኬት ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ ይታወሳል::

ተለጣፊው ቅንጅት ገና ከጥዋቱ ፤በቅንጅት ስም በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ማንም ሰው መግለጫ መስጠት አይችልም፤ ብሏል:: ይህንን አስመልክቶ አቶ ብርሀነ መዋ የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ቃል አቀባይ ለቪኦኤ የአማርኛ ክፍል በሰጡት ቃለ ምልልስ፤ ኢህአዴግም ቅንጅት እንዳይንቀሳቀስና መግለጫ እንዳይሰጥ ካገደው ቆይትዋል፤ የሱ ደጋፊዎች ተመሳሳይ ፍላጎት ቢኖራቸውም አያስደንቅም ብለዋል::

---

በተያያዘ ዜና በኢትዮጵያ የለጋሽ ሀገሮች ቡድን ተለጣፊውን ቅንጅት ደግፈዋል:: እነኚሁ የለጋሽ ሀገሮች አምባሳደሮች ባወጡት መግለጫ፤ የቅንጅት መሪዎች እንዲፈቱ የማይፈቱ ከሆነ ግን ነፃና ፈጣን " Fair and Speedy Trial" እንዲያገኙ ብለዋል:: እስከ አሁን ድረስ ይህ ቡድን የቅንጅትን መሪዎች የህሊና እስረኛ ሲል አልተደመጠም::

## ሀገር ቤት

### ቆራጥ የአዲስ አበባ ተመራጮች ደባውን አከሸፉ

በአቶ አየለ ጫሚሶ የሚመራው ቡድን የአዲስ አበባን መስተዳደር ለመረከብ የሚያደርገው ጥረት ለስድስተኛ ጊዜ ከሸፈ:: ይህ ቡድን ከሰባ በላይ ተመራጮችን አስመዝግብያለው፤ ምክር ቤቱንም ልረከብ ነው ያለ ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምርጫ ቦርድ የተመዘገቡት ተመራጮች ብዛት 68 ነው ከነዚህ መሀከልም ስምንት የሚሆኑት እራሳቸውን ማግለላቸውን በደብዳቤ ገልፀዋል ብሏል:: በደብዳቤ እራሳቸውን ማግለላቸውን ከገለፁት ውስጥ

1. አቶ ዮሴፍ ገብረማርያም
2. አቶ ሲሳይ አዲስ
3. ወ/ሮ እታለማሁ ወርቁ
4. አቶ ዘውዴ ክፍሌ
5. አቶ አሸናፊ ደስታ
6. አቶ ሲሳይ ካሴ
7. አቶ ኤልያስ ሰይፉ
8. ወ/ሮ ላቀች ደገፉ

ይገኙበታል:: እነዚህና ሳይመዘገቡ የቀሩ ተመራጮች የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት ለማሟላት ቆርጠው መቆማቸውን በተግባር አስመስክረዋል::

የአቶ አየለ ቡድን ከኢህአዴግ የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር ተመራጮችን በማስፈራራትና በማባበል ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ውጤቱ ግን አላማረለትም:: በተለጣፊው ቅንጅት የምክትልነት ቦታ የተሰጣቸው አቶ አየለ ጫሚሶ፤ ከንቲባ የመሆን ህልማቸው ያበቃለት ይመስላል::

አቶ አየለ ጫሚሶ ከጀርመን ራዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤ ምክርቤቱን ከተረከብን ለጋሽ ሀገሮች ለከተማዋ ማሳደጊያ እርዳታ ይሰጡናል፤ ይህ ዕድል እንዳያመልጠን ሲሉ የተደመጡ ሲሆን፡ የፖለቲካ ተንታኞች ሁኔታውን ሲተቹ እርዳታው የሚሰጠው ለፖለቲ ጥቅም እንጂ እውነት ህዝቡን ለመደገፍ እንዳልሆነ ያሰያል ብለዋል::

ፓርላማው የወሰነው ቀነ-ገደብ አልፎም ቢሆን ተመራጮችን ምርጫ ቦርድ ይመዘግብ የነበረ ቢሆንም ጭርሱኑ የተመዝጋቢዎች ቁጥር ከመጨመር ይልቅ እየቀነሰ ሄዷል:: በዚሁ መሰረት ተሸናፊው ፓርቲ ኢህአዴግ በ "ባለሞያዎች" ስም የአዲስ አበባን መስተዳደር ይረከባል ተብሎ ይጠበቃል::

# ርዕሰ-አንቀጽ

## የማያድግ ልጅ

ኢህአዴግ፤ ልክ እንደሌሎች አምባገነን መሪዎች ሁሉ፤ የህዝብ የሆነ ነገር ያስፈራዋል:: ስልጣን በጉልበት በጨበጠ ማግስት፤የሀገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት አፈራርሶ ለራሱ ብቻ በሚታዘዝ የፓርቲ ሰራዊት ተክቶታል:: በሀገሪቱ የሚገኘ-ትን ህዝባዊ ተቋማት በአጠቃላይ /የመምህራን ማህበርና የሰራተኞች ማህበር የመሳሰሉትን/ ተለጣፊ አቋቋመባቸው:: በመቀጠልም ከኢህአዴግ በፊት የተቋቋሙትን የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ በአንድ ተለጣፊ አቋቋመላቸው:: አሁን በቅርቡ እንክዋን ለኦብኮ ተለጣፊ ኦብኮ ኢህአዴግ ሰርቷል::

የኢህአዴግ ባለሙያዎች፤ እንደለመዱት ለቅንጅትም ተለጣፊ ቀምመውለታል:: ተለጣፊው ቅንጅት እጅ በዛበትና እርስ በራሱ የተምታታ መግለጫዎች ተደምጠዋል:: ምርጫ ቦርድ ተለጣፊውን አዲስ ፓርቲ ሲለው፤ መስራቾቹ ደግሞ አይደለም ቅንጅት ዕውቅና አገኘ እንጂ የቀድሞው ነው ይሉናል:: የውጭ ዲፕሎማቶች ደግሞ
"የሚያድግ ልጅ" ዓይነት ሙገሳቸውን ለግሰውታል::

እዚህ ላይ ህዝብ ምን ይላል ብሎ ቆም ብሎ ለመጠየቅ አልተሞከረም:: መሰረታዊው ችግርም ተለጣፊው ቅንጅት ወሳኝ የሆነው የህዝብ ድጋፍ የሌለው መሆኑ ነው:: እንዲያውም መሪዎቹ ለስልጣን ሲሉ የህዝብን ድምፅ ወደ ጎን ያሉ፤ በእስር የሚገኙትን መሪዎች አደራም የከዱ ናቸው::

የተለጣፊው ቅንጅት ሌላው ችግር ደግሞ አመሰራረቱ ነው:: ቅንጅት የተመሰረተው በአራት ፓርቲዎች ውህደት ሲሆን፤ ተለጣፊው ግን በቅጡ 1500 ባልሞሉ ግለሰቦች ነው::

አብዛኛው የቅንጅት አመራር በእስር በሚገኙበት ሁኔታ ከ35 በላይ የሚሆኑ የቅንጅት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚገኙበት ሁኔታ፤ ጥቂቱ ለስልጣን ጥቅም ሲል ቀሪው ደግሞ በፍርሀትና በመታለል ተለጣፊውን መመስረት ምን ያህል ከህዝብ የራቀ እንደሆነ ያመለክታል::
ኢህአዴግ እንደለመደው ለቅንጅትም ተለጣፊ እንደሚመሰርት የተጠበቀ ነው:: ይህ ሁኔታ ግን ትግሉን ለአፍታም ቢሆን ወደ ኋላ የሚጎትተው አይሆንም::

## የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከፍተኛ ባለስልጣን የኢትዮጵያን የሰብዓዊ መብት አያያዝን ወቀሱ

ወ/ሮ ሉዊስ አርቦር የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ናቸው:: ቤዝነው ሳምንት ኢትዮጵያ ውስጥ ለአራት ቀናት ያህል የሥራ ጉብኝት አድርገዋል:: በጉብኝታቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ያናገሩ ሲሆን፤ ቃሊቲ ድረስ በመሄድም ስድስት ያህል የቅንጅትን ከፍተኛ አመራር አባላትን አነጋግረዋል:: ከነዚህ ውስጥም ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል የቅንጅት ሊቀመንበርና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ይገኙበታል::

በጉብኝታቸው መጨረሻ ላይ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳብራሩት፤ የኢትዮጵያን የሰብአዊ መብት አያያዝ፤ እጅግ አስፈሪ ብለውታል:: በተለይም የቃሊቲ እስር ቤት አያያዝ አሳሳቢ ነው ብለዋል:: ከ300 በላይ እስረኞች በአንድ ክፍል ይገኛሉ፤ ንጽህናው የተጠበቀ አይደለም:: በተለይ ከሁሉም ያሳዘናቸው ሴቶቹ በታሰሩበት ክፍል ውስጥ ህፃናት ልጆቻቸውን አብረው ማየታቸው ነው:: የቅንጅት መሪዎች በሀገር መክዳት ወንጀል በመታሰራቸው የሞት ፍርድ ሊጠብቃቸው ይችላል፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ምንም አይነት የመለሳለስ አዝማምያ አላሳዩኝም ብለዋል::

## ቃሊቲ

### በቃሊቲ ፖሊሶች በግምገማ ተወጥረዋል::

ከወደ ቃሊቲ ምንጮቻችን እንዳደረሱን ዜና ከሆነ ጠባቂዎች ሰሞኑን በግመገማ ተወጥረው ነው የከረሙት:: ከወህኒ ቤት ምስጢሮች እየሾለኩ ነው ፤ደብዳቤዎች ሳይቀር አምልጠው ይወጣሉ የሚሉት ከክሶቹ መሀል ይገኙባቸዋል:: የቅንጅት መሪዎች የረሀብ አድማ ሲያደርጉ እንደነበር እያወቃቹህ አልተናገራቹህም ተብለዋል:: እንደምንጮቹ ዜና መሰረት፤ ስለረሀብ አድማው የተናገሩት ጠባቂዎች ሶስት ብቻ ናቸው:: በዚህም ምክንያት የወህኒ ቤቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሳይቀር በግምገማው ተወርፈዋል::

ተያይዞ የደረሰው ዜና እንደሚያስረዳው ከሆነ፤ የቅንጅት መሪዎች በጠባቂዎቹ ዘንድ ከበሬታን እያተረፉ ናቸው:: ከእስረኞቹ መሀከል ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ስለእስራቸው ምክንያት ለጠባቂዎቹ ሲያስረዱ፤ " መታሰራችን የእናንተ ጥፋት አይደለም፤ እኛ የታሰርነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ስንል ነው፤ እናንተንም ጨምሮ" ብለዋቸዋል:: ይህ አባባል በጠባቂዎቹ ዘንድ አመኔታንና ከበሬታን አትርፈውላቸዋል::

---

## ግልፅ ደብዳቤ ለአምባሳደር ቪኪ ሃድልስተን

### ብርቱካን ሚደቅሳ - ቃሊቲ ወህኒ ቤት

የሕግ ተማሪ ሳለሁ ነገሮችን ሁሉ በከፍተኛ ትኩረት እመለከት በነበረበት ነገር ግን የማጠናውን ጠጣር ትምህርት ለመረዳት ተቸግሬ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስና ካርታ ሲጠፋኝ፣ ካለሁበት አዘቅት ከፍ የሚያደርገኝ የሚያወጣኝ መሰላል ሳጣ ዘወትር ብር ብዬ ወደ ዩኒቨርሲቲው የሕግ ቤተ መጻሕፍት እሔዳለሁ:: በዚያም ፈጥኜ የመጣሁበትን ጨለማ የሚያስረሳ የብርሃን ማማ ላይ እወጣለሁ:: በዚህ ሥፍራም ጥበቃ ባልበዛባቸውና እዚህም እዚያም በተዝረከረኩ መጻሕፍት ተከብቤ ከአንድ ፍፁም አርዓያ ከሆነኝ አሜሪካዊ ጀግና ጋር ተዋወቅሁ፤ ከስመ-ጥሩ ዳኛ ኦሊቨር ዌንደል ሆልምስ ጋር...

ዳኛውን ስተዋወቀው በጥበብና በብልሃት የተመላ፣ ሊቀ-ሊቃውንት ረቂቅና ጥልቅ ነበር:: ብሉይ (ዘመን-አይሽሬ) ደብዳቤዎቹ እና መፃሕፍቶቹ ከሕግም በላይ እጅግ ይልቁ ነበር:: ታላቁ ሰው ታላቅ የመሆንን መልካምነት አምነን ለታላቅነት እንድንነሳ፣ በመከራችንና በፈተናችን መሃል ብርቱ ማሰብና መተግበር ለሕልውናችን አስፈላጊ መሆኑን፣ መልካም ወግና ልማዳችንን ሳንንቅ ለመለወጥ እንድንደፍር አይዟችሁ ይለናል:: እስካሁንም ድረስ ዘወትር ከአፌ የማይጠፉ የዳኛው ተጠቃሽ ንግግሮች አሉ:: ከነዚህም መሃል ዳኛው ካደረጓቸው ንግግሮች ባንዱ ከተናገሯቸው መሳጭ ጥቅሶች እነሆ... «ሞት ጆሮዬን እየጎተተ እንዲህ አለኝ... እየመጣሁ ነውና ኑር!»

ባለፈው ዓመት ግንቦት 7 በዚያ በሚለበልብ የጥዋት ፀሐይ «ደግሞ ምን ይመጣ ይሆን?» እያሉ ልክ

እንደ ወታደር የፍፃሜውን መጨረሻ ያዩና ክቡርነቱም ድንገተኛ መሆኑን የተረዱ ኢትዮጵያውያን

በተስፋ ለመኖር መረጡ:: የፖለቲካ ስርዓቱን ከልባቸው አምነው በትዕግስት ረጅም ሰልፍ ተሰልፈው ዕድል ፈንታቸውን ለመወሰን በፅናት ተጋደሉ:: በወቅቱ ተከፍቶ የነበረው የፖለቲካ ድርሻ አንዳንዶች ሊናገሩት እንደሚደፍሩት ያን ያህል ወለል ያለ አልነበረም:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ገርበብ ተደርጎ በተከፈተው በር ገቡ:: (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

**ድምፅ**

በቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ የሰሜን አሜሪካን ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ የህዝብ ግኑኝነት ክፍል እየተዘጋጀች የምትወጣ ናት:: ያለዎትን አስተያየትም ሆነ ጽሁፎች በአድራሻችን:-

ድምፅ
766 Rock Creek Church Rd.
Washington Dc, 20010
ይላኩልን::
ስልክ 202 541 9507
ፋክስ 202 541 1090
dimtse@kinijit.com

## የሀገር ፍቅር ልክፍት

ዶ/ር ሀይሉ አራያ

ከናቴ ማህፀን ነው፤ ስፈጠር ከጥንቱ፤
ከህይወት መስመሩ፤ ከአገናኝ
ከእትብቱ፤
ወይስ ከእናቴ ጡት፤ከአይኖችዋ
እይታ፤
ከየት ነው ያገኘኝ፤ ከቶ ከምን ቦታ፤
ያገር ፍቅር ልክፍት፤ ያገር ፍቅር
በሽታ፤

.
.
.

ቄስ ት/ቤት ይሆን፤ ከየኔታ ቤት ታዛ፤
"ሀሁ" ስል "ለሉ" ስል፤ ፊደልን ሳበዛ?
በቀለም በፊደል፤ በነጥብ ተመስሎ፤
በውስጤ የገባ፤ ዓይነኩሌ ከፍሎ፤
ወይስ ውሎ አድሮ ነው፤ከፊደል በኋላ?
የኔታን ሄድኩኝ ብዬ፤ ስገባ ከአስክዋላ?
ገባ ከጆሮዬ፤ተመስሎ ዜማ፤
"ኢትዮጵያ ሆይ!" ብለው ሲጠሯት
ስሰማ፤
"ተጠማጅ አርበኛ፤ባገር መውደድ
ቀንበር";
ለሶስቱ ቀለማት፤ በሰልፍ ሲዘመር፤
አረንጓዴ ቢጫ፤ ቀይ ቀለም ባንዲራ፤
ስትወጣና ስትወርድ፤ ስንዘምር በጋራ?

(ከገጽ 2 የዞረ)

ጫጫታ ከነበረባቸው በአንዱ ሰልፍ ላይ እኔም ድምፄን ለመስጠት ተራዬን እየጠበቅሁ ነበር:: ዞር ስል ቁርጠኝነት የሚነበብባቸው የተከበሩ አዛውንት አየሁ:: ዓይናቸው በእምባ ተሞልቷል፤ አካላቸው በደስታ ይርድና ይንቀጠቀጥ ነበር:: ሰውዬው ሁሉን ያዩ ናቸው:: ነገር ግን የዚያን ዕለቱ ተመክሯቸው ለአዛውንቱ እንግዳና አዲስ ነበር:: ከእሳቸው በተጨማሪ በሰፈሬ በግድ የለሽነቷ የማውቃት ወጣት ሴት የተወነችው ከተለመደው ወጣ ያለ ትዕይንት ቀልቤን ሳበው:: ወጣቷ የደከሙ የዕድሜ ባለጠጎችን የማዘል ያህል እየደገፈች ወደ ድምፅ መስጫው ታደርስና ትመለስ ነበር:: እነዚህን በጥልቅ ስሜት የተሞሉ ታላቅ ክስተቶች ለማስተዋል መታደል ልብ የሚነካ ነበር:: በዕለቱ ባየኋቸው እነዚህና ሌሎች መሰል ነገሮች ሁሉ እውነተኛ ሰላሜን እና ፍፁም ደስታን አግኝቻለሁ:: በግንቦት 7 ፓርቲዬ በአፀፋው ካገኘው ወይም እንዳያገኝ ከተከለከለው ድል ይልቅ ኢትዮጵያውያን ለሲቪክ ባህል እና ለተስፋቸው ዕውን መሆን ያሳዩትን ጽናት እና ቁርጠኝነትን አስበልጬ እመለከተዋለሁ::

ፖለቲካዊ አስተሳሰቦችና አቋሞች ብዙ ጊዜ የአመክንዮ ተሞክሮዎች ናቸው:: ቅንጅት በግንቦት 7ቱ ምርጫና ከምርጫው አንድ ሳምንት በፊት ከነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ልምድና ተሞክሮ በመነሳት በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሽምጋይነት የተካሄዱ ድርድሮችና ውይይቶች ከምርጫው በኋላ ፓርቲው ለወሰዳቸው እርምጃዎች መነሻና መሰረቶች ነበሩ:: እኛ የኢትዮጵያውያን ተስፋ እንዲሞት ልንፈቅድ አይቻለንም:: ማዳም አምባሳደር ለመጀመሪያ ጊዜ በመስከረም ወር ላይ ታቅዶ የነበረውን ሰላማዊ ሰልፍ መሰረዝ አስመልክተው፤ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክትዎን ሲያስተላልፉ የነገርኩዎትም ይህንኑ ነበር:: እኛ የኢትዮጵያውያን ተስፋ እንዲሞት አንፈቅድም ብዬ...

በዚያን ቀን በቅን-ኀሳብ፤ በመልካም ምግባር እና በግርማ ሞገስ ተመልተው ነበር:: በዕለቱ ቤቴ ስገባ ስለ እርስዎ ያለኝን መረጃና መዝገብ ሳገላብጥ ታላቅ ዲፕሎማትነትዎንና ለዓመታት አገርዎን ከፍ ባለ ማዕረግ በትጋት ማገልገልዎን ተረዳሁ:: አገልግልዎትዎንም በታማኝነት እና

በብቃት እንደሚፈፅሙ አወቅሁ:: ለመስከረም 23 ተጠርቶ የነበረውን ቤት የመቀመጥ ጥሪ እርስዎ በተገኘ ብት አስቸኳይ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ አድርገን ከብዙ ክርክር በኋላ ተሰረዘ:: ፓርቲው ሥራውን እንዴት እንደሚሰራ፣ ምን ያህል ዴሞክራቲክ እንደሆነ፣ መሪዎቹ ሰላማዊ እና ፋይዳ ያላቸው መሆናቸውን በቅርበት አስተውለዋል:: ለእርስዎም ለተሰጥዎት አመኔታም ግሉ-ምስክር ሊሆኑ እንደሚችሉ አውቃለሁ:: ይህን ታማኝ እና ቅን ሽምጋይነትዎን ይዘው ቢቆዩ እመኝ ነበር::

(ተከታዩን በሚቀጥለው ዕትም ይዘን እንቀርባለን)

## ኢህአዴግን በማይገባው ቋንቋ ማናገር

አምባገነኖች የህዝብ ድምፅ አይሰማቸውም:: ከህዝብ ስላልሆኑ ፤የህዝብ ስላልሆኑ:: ስልጣናቸውን ያገኙት በጉልበት እንደመሆኑ መጠን ስልጣናቸውንም የሚያስጠብቁት በጉልበት ነው:: የህዝብ አመኔታ ስለሌላቸውና እነሱም ህዝብን ስለማያምኑ፤ በሀገሪቱ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ባጠቃላይ አፍነው ይይዛሉ:: የሀገሪቱ የጸጥታ ሀይሎች ህገ-መንግስቱንና ዳር ድንበር ማስከበር ትተው ስራቸው የአምባገነኖችን ስልጣን መጠበቅ ይሆናል:: የመንግስት ሚዲያዎች ለህዝብ መረጃ ከማቀበል ይልቅ የመንግስት የፕሮፓጋንዳ መሳርያ ይሆናሉ:: የግል ፕሬስ፤ ታማኝ ከሆኑት በስተቀር እስከነጭርሱ የሉም:: የፍትህ ተቋማት በዋነኛነት፤ መንግስት ህዝብን የሚያፍንበት ተቋማት ይሆናሉ::

የዓለም ታሪክ እንደሚያስረዳው፤ እንደዚህ አይነት አምባገነን መሪዎች ሁልጊዜም ተቃውሞ ያጋጥማቸዋል:: ህዝብ በተለያየ መንገድ፤ በጋራም ሆነ በተናጠል፤ እምቢ አልገዛም ማለቱ የማይቀር ነው:: የተቃውሞው መንገድ እነደየጊዜውና እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ቢለያይም ሰላማዊና የትጥቅ ትግል ተብለው ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ:: አምባገነን መሪዎችን በትጥቅ ትግል ማስወገድ አይቻልም ባይባልም፤ የትጥቅ ትግሉን ከባድ ሊያደርጉት ከሚችሉት ነገሮች አንዱና ዋነኛው አምባገነኖቹን በሚያውቁት ቋንቋ ማናገር ስለሚሆን ነው:: ስልጣናቸውን ለማጠናከር ስለሚፈልጉና የስልጣናቸው ምንጭ ጠመንጃ ስለሆነ፤ የሀገሪቱን ሀብት ባብዛኛው የሚያውሉት የጦር ሀይሉን በመገንባት ነው:: የትጥቅ ትግሉም፤ ባንፃራዊ መልኩ፤ የሰለጠኑበት ነው:: አምባገነኖች የማያውቁትና የማይገባቸው ቋንቋ ቢኖር፤ የስልጣናቸው ምንጭ ያልሆነው፤ ህዝባዊ አመጽ ነው:: ህዝባዊ አመጽ፤ መስዋዕትነቱ ከትጥቅ ትግል ያነሰ ወይም የከፋ ሊሆን ይችላል:: ውጤቱ ግን አንድን መንግስት በሌላ /ምንአልባትም የባሰ አምባገነን/ መለወጥ ብቻ ሳይሆን፤ በሀገሪቱ ውስጥ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚኖርበትን ስርዓት ጭምር መመስረት ነው::

ህዝባዊ ሰላማዊ ትግልን፤ ባነሰ መስዋዕትነትና በፈጠነ መልኩ ውጤት እንዲያመጣ ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድና ስልት መንደፍ እጅግ ወሳኝ ነው:: በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ጠንቅቆ ማወቅና የራስን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል:: የኃላ ኃላ የሀገሪቱ የፀጥታ ኃይሎች የትግሉን ዓላማ ተረድው፤ የአምባገነኖች መሳርያ ከመሆን ይልቅ፤ትግሉን እንዲቀላቀሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

ቅንጅት በህዝብ የተመረጠ ሀይል እንደመሆኑ መጠን፤ ህዝባዊ ትግሉን የመምራት ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት:: የቅንጅት ትልቁ ጥንካሬ የህዝብ ድጋፍ ያለው መሆኑ ነው:: የኢህአዴግ ትልቁ ድክመቱ ምንም የህዝብ ድጋፍ የሌለው መሆኑ ነው:: በዚህ የሀይል ሚዛን ስልት መሰረት፤ህዝብና ቅንጅት የትግሉን አካሄድ መምራትና ኢህአዴግ ደግሞ ላለመሞት ሲፍጨረጨር መታየት አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ ብቸኛው መንገድ ኢህአዴግን በማይገባው ቋንቋ ማነገር ብቻ ነው::